| | |
|---|---|
| ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ<br>ኢየሱስ ክርስቶስ<br>ካህኑ ለዓለም፥ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ<br>ንጉሠ ጽዮን <u>ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u><br>The Conquering Lion of the Tribe of Judah<br>Jesus Christ<br>Eternal Priest, King of Zion and<br>King of Kings of Ethiopia | ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር<br>ድንግል ማርያም<br>እሙ ለአምላክነ ወእምነ ዘዚአነ፥<br>ንግሥተ ጽዮን፥ <u>ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u><br>Ethiopia stretches out Her Hands to God<br>The Virgin Mary<br>Mother of God and Our Holy Mother<br>Queen of Zion and Ethiopia |

# <u>ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።</u>

**ኢየሱስ መሢሕ ኢትዮጵያዊ፡**
**አንሶሰወ ገሃደ፤ ወአስተርአየ ከመ ሰብእ፤**
**በበሕቅ ልኅቀ፤ በሠላሳ ክረምት፡ በዮርዳኖስ ተጠምቀ።**

**ይድረስ፡ ለተከበሩና ለተወደዱ መልአከ መንክራት ግርማ ወንድሙ።**
**አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ።**

ከነቤተሰብዎና ከአገልግሎት ባልደረቦችዎ ጋር፡ እንደምን አሉ? አገራችን ኢትዮጵያ በኾነችው፡ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ምክንያት፡ እግዚአብሔር፡ በምልዓት ባስገኘልን የቸርነት ልግሥናው፡ ለዘወትርና ለዘለዓለሙ ይክበር ይመስገን፡ እኔ፡ ከኪዳናውያንና ኪዳናውያት ቤተሰቤና የአገልግሎት ባልደረቦቼ ጋር ደኅና ነኝ።

ባለፈው ዓመት፡ በአዲስ አበባ ደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ዐፀደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያካኺዱት በነበረው ክህነታዊና ተአምራዊ የጉባኤ አገልግሎትዎ ላይ፡ ባለቤቴ፡ ኪዳናዊት እመቤት ራሔል ዘካርያስ፥ እንዲሁም፡ ከልጆቻችን መካከል፡ ኪዳናውያት እመቤታት ትምህርተ ኤርምያስና ስብከተ ኤርምያስ፥ ኪዳናዊ አበቤት ሰማዕተ ኤርምያስም ተገኝተው ስለነበረ፡ እርስዎ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን መሠረት ከሚሰጡት የምሥራች ትምህርትዎና ስብከትዎ፥ ይልቁንም ትንግርታዊ ከኾነው፡ ከምግባራዊው የንስሓና የፈውስ ተልእኮዎ፡ መንፈሳዊዉን ጸጋና በረከት ሊሳተፉ ችለው እንደነበረ ላስታውስዎ እወድዳለሁ።

እነርሱም፡ በዚያን የዕለቱ ጉባኤ ላይ፡ በዚህ መልክና ይዘት፡ መገኘትና መሳተፍ ብቻ ሳይኾን፡ ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ተዘጋጅተውና ታትመው፡ ለሕዝብ እየተሠራጩ ያሉት መጻሕፍቴን፡ አበርክተውልዎ ስለነበረ፡ የየግል አስተያየታቸውን፡ ለጉባኤው ያካፍሉ ዘንድ፡ ወደመድረኩ በመጋበዛቸው፡ መናገራቸውን፥ እርስዎም፡ የበኵልዎን አበረታች ምዕዳን በመስጠት ያስሰሙት ቃል፡ ኹሉም፡ በመቅረጸ-ሥዕል ተመዝግቦ ስለነበረ፡ መዘክሩን ተመልክቼውና ሰምቼው፡ ደስ ከመሰኘቴ ጋር፡ ለፈጣሪዬና ለቅድስት እናቱ፡ ምስጋናዬን አቅርቤአለሁ።

ከዚህ ጋር፡ "'በማለዳ መያ'ዝ!' የክፉ መንፈሶች ድርጊት! ቅጽ ፩" በሚል ርእስ የደረሱት መጽሓፍዎ፡ ስምዎና ጽሑፍ ኪዳንዎ ሠፍሮበት፡ በየካቲት ፲ ቀን፥ ፳፻፫ ዓመተ-ምሕረት በተጻፈ ማስታወሻ፡ በስጦታ ስለላኩልኝ፡ ደርሶኝ፡ "እግዚአብሔር ይስጥልኝ!" ብዬ፡ በምርቃት ተቀብዬ፡ ከተመለከትሁት በኋላ፡ መንፈሳዊ እርካታን ስላገኘሁበት፡ ይህን ደብዳቤ እጽፍልዎ ዘንድ፡ መነሻ ኾነኝ።

የዚህን መጽሓፍዎን ኹነኛ መልእክት፡ በአጠቃላይና በአጭር ቃላት ወስኜ ላቀርበው ስሞክር፡ መላውን ዓለም፥ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውንም ትውልድ በሚመለከት፡ ኹለቱም ወገኖች የሚገኙበት፡ የጊዜያችን ነባራዊና ምትሓታዊ ኹኔታ፡ አካል ገዝቶ የተንጸባረቀበት ኾኖ አግኝቼዋለሁ፤ ይኸውም፡-

-በአጠቃላይ መልኩና ይዘቱ ሲመዝኑት፡ ለመላው የሰው ዘር፥ በተለይም፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ የትውልድና የህልውና ግንዶች ከኾኑት፡ ከአዳምና ሔዋን ዘመን ጀምሮ፡ በመንፈስ ቅዱስ ባለቤትነትና የበላይነት ተጠብቃ ለምትመራው፡ ለእውነተኛዪቱ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በሥውርና በግልጽ፥ በረቂቅና በግዙፍ፥ ተፃራሪ ከመኾን ያልቦዘነው፡ መንፈሳዊዉና ሰብኣዊው የክፉት ወገን፡ እስከዛሬና ዛሬም፡ እየፈጸመና እያካኼደ ያለው የጥቃት ዘመቻ፡ በእርሱ፡ አስመሳይ አሸናፊነት፡ እያደገና እያየለ፥ እየሰፋና እየተንሰራፋ የሚኼድ መስሎ የታየበት መኾኑ ነው።

-በአጭር መልኩና ይዘቱ ሲመዝኑት ደግሞ፡ የመጽሓፍዎ መልእክት፡ ከዚህ የሚከተሉትን ቍም ነገሮች ይዞ መገኘቱን አረጋግጦ ያመለክታል፡-

-የጥቃቱ ዘመቻ፡ ምንጊዜም ቢኾን፥ በመጨረሻና ለዘለዓለሙም፡ የሚያበቃው፡ በእውነተኛዪቱ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ድል አድራጊነት፥ በክፉቱም ወገን ሽንፈት መኾኑ መታወቁ ነው፤

-አምላከ ኢትዮጵያ፡ እንዲህ የተጋድሎ ሰማዕትነትን አካኺደውና አከናውነው እንዲፈጽሙለት፡ ትሑትና ታማኝ፥ ቆራጥና ጽኑ የኾኑትን፡ እርስዎን፡ አገልጋዩን፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ለዚህ ተልእኮ፡ መርጦና አዘጋጅቶ፡ በሓዋርያነት መላኩ ነው፤

-"ለምን ላከዎ?" ለሚለው ጥያቄ፡ መልሱ፡ ለእግዚአብሔር እውነት ደጋፊዎችም ኾነ ተቃዋሚዎች፡ ግልጽ መኾኑ ነው፤ ይኸውም፡-

-በአንድ በኩል፡ የክፉው መንፈስ ኃይል፡ የጨለማ ግዛቱንና የሓሰት ሥልጣኑን፡ በመላው ዓለምና በኢትዮጵያ፡ እስከምንና የት ድረስ፡ ሥር በሰደደ ምትሓታዊ መጠንና ጽናት፡ አስፋፍቶና አጠናክሮ እንደሚገኝ፡ ለፍጥረቱ ኹሉ፡ በገሃድ ሊያሳይና ሊያሳውቅ መኾኑ ነው፤

-በሌላው በኩል ደግሞ፡ ይኸው የክፉው መንፈስ ኃይል፡ የዚሁ፡ የጨለማ ግዛቱና የሓሰት ሥልጣኑ ዘመን፡ የነፃነት አክሊልን ተቀዳጅታ፡ የቀስተ ደመና ጋሻዋ የኾነውን ሰንደቅ ዓላማዋን በተጐናጸፈችው ኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያምና በድል አድራጊው ባለዘውድ ኢትዮጵያዊ አንበሳ ልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንጸባራቂ ብርሃንና ደምሳሽ ኃይል እየተነነና እያከተመ መኼዱን ሊያበሥርና ሊያረጋግጥ ነው።

እንግዴህ፡ መልሱ፡ ይህ ከኾነ፡ ይኸው ተልእኮዎ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ አንዱ የአገልግሎት ዘርፍ በመኾኑ፡ በበኩልዎ ጸንተውበትና ተጠናክረውበት እንደሚቀጥሉበት በማመን፡ ላበረታታዎ እወድዳለሁ። ደግሞም፡ በዚችው፡ በዘለዓለማዊቷ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልግሎት ላይ የምንገኝ፡ እኔና እኔን የመሰሉት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ኹሉ፡ ገድለኛ በኾነው፡ በዚሁ ተልእኮዎ፡ በየበኩላችንና በያለንበት፡ ዐብረንዎት የተሰለፍን መኾናችንን ሳረጋግጥልዎ ደስ ይለኛል።

የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና የእመ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም በረከት፡ ከኹላችን እንደማይለየን እናምናለን።

ጥር ፲፰ ቀን፥ ፳፻፮ ዓመተ ምሕረት።

በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን፡ የተልእኮ ተባባሪዎ፡-

---

ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ።